መልዕክት አምስት

**በኤፌሶን መጽሐፍ የተገለጠው የመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊው እደላ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡ ኤፌ. 1፡3-14፤ 2፡18፤ 3፡16-19፤ 4፡4-6፤ 5፡19-20፤ 6፡10-11፣ 17

**I. በቅዱሱ ቃል ውስጥ የተገለጠው ሦስታንዱን አምላክ የሚመለከተው መገለጥ ለአስተምህሯዊ መረዳት ሳይሆን እግዚአብሔር ወደ መረጣቸው እና ወደ ተቤዣቸው ሰዎች ውስጥ ለልምምዳቸው እና ለድሰታቸው እርሱን በመለኮታዊው ሥላሴው ለማደል ነው—2ቆሮ. 13፡14፡-**

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ሦስታንዱ አምላክ የእምነታችን ነገር ብቻ እንዳልሆነ ይገልጣል፤ በውስጣችን በማደር እና ንደ ሕይወታችን እና እንደ የሕይወት አቅርቦታችን ራሱን ወደ ውስጣችን በማደል እርሱ ለኛ ውስጠ-ልምምዳዊ ነው—ሮሜ. 8፡2፣ 6፣ 10-11፡፡

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው ሦስታንዱ አምላክ ወደ መረጣቸው እና ወደ ተቤዣቸው ሰዎች ውስጥ እንደ ሕይወታቸው እና የሕይወት አቅርቦታቸው ራሱን ለመሥራት ባለው ገገር መርህ መሠረት ነበር—መዝ. 36፡8-9፡፡

**II. መለኮታዊው ሥላሴ የመላው መጽሐፍ ቅዱስ መዋቅር ነው፤ መላው መጽሐፍ ቅዱስ፣ በተለይ ደግሞ የኤፌሶን መጽሐፍ፣ በመለኮታዊው ሥላሴ የተዋቀረ ነው፡-**

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እያንዳንዱ ምዕራፍ በመለኮታዊው ሥላሴ እንደ መሠረታዊ ንጥረነገር የተገነባበት ብቸኛው መጽሐፍ የኤፌሶን መጽሐፍ ነው፡፡

ለ. ሦስታንዱን አምላክ ካላወቅን፣ የኤፌሶንን መጽሐፍ ጥልቅነት መረዳት አንችልም፣ ምክንያቱም የዚህ መጽሐፍ እያንዳንዱ ምዕራፍ መለኮታዊውን ሥላሴ እንደ መዋቅር የያዘ ነው—1፡3-14፤ 2፡18፤ 3፡16-17፤ 4፡4-6፤ 5፡19-20፤ 6፡10-11፣ 17፡፡

**III. የቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ አካል መፍራት፣ መኖር፣ ማደግ፣ መገንባት እና መዋጋትን በተመለከተ በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ ያለው መላው መገለጥ በመለኮታዊው ኢኮኖሚ እና ወደ ክርስቶስ አካል ብልቶች ውስጥ በሚታደለው በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ የተዋቀረ ነው፤ ከዚህም የተነሳ፣ ወሳኙ የኤፌሶን መጽሐፍ ወሳኝ ትኩረት ወደ አማኞች ውስጥ የሚከናወነው የመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊው እደላ ነው፡-**

ሀ. ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔር አብ እንዴት ብልቶቹን በዘላለም ውስጥ እንደመረጠ እና እንደወሰናቸው፣ እግዚአብሔር ወልድ እንደዋጃቸው፣ እና እግዚአብሔር መንፈስ ለመያዣ እንዳተማቸው፣ ከዚህም የተነሳ ሁሉን በሁሉ የሚሞላባት የክርስቶስ አካል ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን መመሥረት ወደ አማኞቹ ውስጥ ራሱን እንደሚያካፍል ይገልጣል—ቁ. 3-14፣ 18-23፡-

1. የኤፌሶን መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ በሂደት ያለፈውን የሥላሴ እደላ እና ከሁሉ በላይ ከፍ ያለውን የክርስቶስን [ወደ ቤተ ክርስቲያን] መተላለፍ፣ የነዚህን የሁለቱን ውጤት ይገልጣል፡፡
2. የእግዚአብሔር አብ እደላ ውጤት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዓላማ ይናገራል (ቁ. 3-6)፣ የእግዚአብሔር ወልድ እደላ ውጤት የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዓላማ መፈጸም ይናገራል (ቁ. 7-12)፣ የእግዚአብሔር መንፈስ እደላ ውጤት ደግሞ የተፈጸመውን የእግዚአብሔር ዓላማ ትግበራ ይናገራል (ቁ. 13-14)፡፡
3. ከሁሉ በላይ ከፍ ያለው ክርስቶስ የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ ስለሆነ፣ ከሁሉ በላይ ከፍ ያለው [ወደ ቤተ ክርስቲያን] መተላለፉ የሦስታንዱ አምላክ የበለጠገ እደላ በሙሉ ያካትታል፤ የሦስታንዱ አምላክ ሦስት እጥፍ እደላ ለሁሉ በላይ ከፍ ያለው የክርስቶስ [ወደ ቤተ ክርስቲያን] መተላለፍ ውስጥ የተካተተ እና ከሁሉ በላይ ከፍ ባለው ክርስቶስ ሁሉን ያካተተ [ወደ ቤተ ክርስቲያን] መተላለፍ የተፈጸመ እና የተጠናቀቀ ነው—ቁ. 15-23፡፡

ለ. ምዕራፍ ሁለት በመለኮታዊው ሥላሴ አማኞች ሁሉ፣ አይሁድም አሕዛብም፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ፣ በእግዚአብሔር ወልድ በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ መድረስ እንደሚችሉ ያመለክታል—ቁ.18፡-

1. ይህም ከተሰግዎ፣ ከስብዕና ኑሮ፣ ከመስቀል፣ እና ከትንሣኤ ሂደቶች ሁሉ በኋላ እንኳን፣ ሦስቱ በአንድ ላይ እንደሚኖሩ እና አንዱ በሌላው ውስጥ በአንድ ጊዜ እንደሚኖር ያመለክታል፡፡
2. በፈፃሚው፣ መንገድ በሆነው በእግዚአብሔር ወልድ በኩል እና በአስፈፃሚው፣ ትግበራ በሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ጀማሪ፣ የድሰታችን ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር አብ መድረስ እንችላለን፡፡
3. እኛ በአብ እንደ ምንጩ፣ በወልድ እንደ መንገዱ፣ እና በመንፈስ እንደ ፍሰቱ እደላ የተፃፍን ግጥም ነን—ቁ. 10፡፡
4. ድንቁን የጥበብ ሥራ ለማግኘት የሆነው የአብ እደላ፣ አዲሱን ሰው ለማፍራት የሆነው የወልድ እደላ ፣ እና በአንድ አካል የመንፈስ እኛን ወደ አብ ማምጣት የቤተ ክርስቲያንን መገንባት እና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መሟላት ያመጣል—ቁ. 10፣ 15-16፣ 21-22፡፡

ሐ. በምዕራፍ ሦስት በእግዚአብሔር መንፈስ አማካኝነት አማኞች ወደ ውስጥ ሰውነታቸው በኃይል መጠንከርን እግዚአብሔር አብ እንዲሰጣቸው፣ ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ወልድ ቤቱን በልባቸው እንዲሠራ፣ ማለትም፣ ወደ እግዚአብሔር ሙላቱ

ልክ ደርሰው እንዲሞሉ እርሱ (ክርስቶስ) መላው ማንነታቸውን ሞልቶ እንዲይዘው ሐዋርያው ይጸልያል፤ ይህ በመለኮታዊው ሥላሴ በእግዚአብሔር ውስጥ የአማኞች ልምምድ እና ተሳትፎ ከፍተኛ ጫፍ ነው—ቁ. 16-19፡-

1. አብ ምንጭ ነው፣ መንፈስ መንገድ ነው፣ ወልድ ግብ ነው፣ የሦስታንዱ አምላክ ሙላት ደግሞ ውጤቱ ነው፡፡
2. ሦስቱም እያንዳንዳቸው ለሦስታንዱ አምላክ ሙላት እንጂ ለየራሳቸው አይሠሩም፤ ይህ የመለኮታዊው ሥላሴ ውብ ስዕል ነው—ተዛ. ማቴ. 12፡28፡፡

መ. የአካሉ ብልቶች ሁሉ መለኮታዊውን ሥላሴ ይለማመዱ ዘንድ በሂደት ያለፈው አምላክ እንዴት እንደ መንፈስ፣ እንደ ጌታ እና እንደ አብ ከክርስቶስ አካል ጋር እንዴት እንደተዋሃዱ ምዕራፍ አራት ይገልፃል—ቁ. 4-6፡-

1. የክርስቶስ አካል ለሦስታንዱ አምላክ መዳበር ክበቡ ነው፡፡
2. እግዚአብሔር አብ ከሁሉ በላይ በመሆኑ የእርሱ መለኮታዊ እደላ፣ ወልድ በሁሉም በኩል በመሆኑ የእርሱ መለኮታዊ እደላ፣ እና መንፈስ በሁሉም በመሆኑ የእርሱ መለኮታዊ እደላ የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ ሦስታንዱን አምላክ እንዲለማመዱ እና እንዲደሰቱ ያስችላቸዋል፡፡
3. እነዚህ ጥቅሶች አራት ማንነቶችን ይገልጣሉ—አንዱን አካል፣ አንዱን መንፈስ፣ አንዱን ጌታ፣ እና አንዱን አምላክ አብ—ሕያውን የክርስቶስ አካል ለመሆን እንደ አንድ ተዋሕደው፤ ከዚህም የተነሳ ሦስታንዱ አምላክ እና አካሉ አራት በአንድ ናቸው፡፡

ሠ. ምዕራፍ አምስት አማኞች ጌታ እግዚአብሔር ወልድን በእግዚአብሄር መንፈስ ዝማሬዎች እንዲያመሰግኑ፣ እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ በእግዚአብሔር ወልድ ለእግዚአብሔር አብ ምስጋናን እንዲሰጡ ይመክራል—ቁ. 19-20፡-

1. ይህ በሂደት ያለፈውን አምላክ እንደ ሦስታንዱ አምላክ እንድንደሰተው እርሱን በመለኮታዊው ሥላሴው ለማወደስ እና ለማመስገን ነው፡፡
2. በመለኮታዊው ሥላሴ መለኮታዊ እደላ አማካኝነት፣ በእግዚአብሔር ውስጥ እንደ ፍቅር እና ብርሃን በመመላለስ እንደ የእግዚአብሔር ልጆች ተቀናብረናል፣—ቁ. 2፤8፡፡

ረ. ምዕራፍ ስድስት ሁሉንም የእግዚአብሔር አብ ዕቃ ጦር በመልበስ፣ እና የመንፈስንም ሰይፍ በመያዝ በጌታ በመበርታት መንፈሳዊውን ጦርነት እንድንዋጋ ያዘናል—ቁ. 10-11፤ 17፡-

1. እግዚአብሔር ወልድ ውስጣችን ያለ ኃይል ነው፣ በወልድ ያወቅነው እግዚአብሔር በላያችን ላይ ዕቃ ጦራችን ነው፣ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው እግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ ሰይፍ ነው፡፡
2. ይህ በመንፈሳዊ ጦርነት እንኳን ሳይቀር የአማኞች የሦስታንዱ አምላክ ልምምድ እና ድሰታ ነው፡፡

**IV. በመላው የስድሳ ስድስቱ መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት መሠረት፣ መለኮታዊው ሥላሴ— አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ—ለእግዚአብሔር እደላ ነው፣ ማለትም፣ ወደ መረጣቸው ሰዎች ውስጥ እግዚአብሔርን ለማሰራጨት ነው፤ ወደ ውስጣችን ራሱን እንዲያድል፣ የክርስቶስ አካል ሆነን መገንባት እንድንችል እንደሰተው ዘንድ እና እርሱ ለዘላለም እስከ ዘላለም እንዲገዛ ለዳግመኛው መምጣቱ የዓለም መንግሥት የጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ትሆን ዘንድ የክርስቶስ ሙሽራ ሆነን እንድንዘጋጅ እግዚአብሔር ሦስታንድ ነው—ራእ. 11፡15፡፡**

© 2022 Living Stream Ministry